# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 283 ጥቅምት 1 2006 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

እኛ ግንቦት ሰባቶች ዘረኛዉንና አሸባሪውንና የወያኔ ስርዐት ለመደምሰስና ህዝብ በነፃነት ያለፍርሃት የሚኖርበትን አገር ለመፍጠር ቆርጠን ተነስተናል። ከእንግዲህ የሚያቆመን ምንም ነገር የለም። የምንታገለዉ ለህዝብ ጥያቄያችንም ህዝባዊ ጥያቄ ነዉና እኛም አንደጥያቄዉ በየመስጊዱ፤ በየቤተክርሲቲያኑና በየሰፈሩ ዉስጥ አለን። እኛ የሌለንበት ስፍራ የለም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ አንዳንድ የአማራ ክልል ከተሞችን ለራሱና ለሌሎች ለአጎራባች ክልሎች ሊሸልም መሆኑ ተሰማ

ከዚህ ቀደም ወልቃይት ጠገዴን ከጎንደር ገንጥሎ ትግራይ ዉስጥ የጨመረዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ያኔ የዘረፈዉ መሬት አልበቃ ብሎት አሁንም በአማራ ክልል የሚገኙ አንዳንድ የድንበር ከተሞችን ወደራሱ ወይም (ትግራይ ክልል) ለመጨመር ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን ኢሰት ቴሌቪዥንና ሬድዮ የአማራ ክልል ባለስልጣናትን ጠቅሶ ዘገበ። የኢሳት ዘገባ በግልጽ እንዳስቀመጠዉ በድንበር አካባቢ የሚገኙ የአማራ ክልል ከተሞች የሚሰጡት ለኢያንዳንዱ አጎራባች ክልል ቢሆንም ወያኔ ይህንን የአማራን ክልል ከተሞች ለአጎራባች ክልሎች ሁሉ የማሽጋሸግ ዕቅድ ያወጣዉ ለይስሙላ እንደሆነና ዋና አላማዉ አማራዉን ለማዳከምና የራሱን ክልል ለማስፋት ነዉ የሚሉ ብዙዎች ናቸዉ። በድንበር አካባቢ ከሚገኙ የአማራ ክልል ከተሞች አስተዳዳሪዎች በተገኘው መረጃ መሰረት የጃን አሞራ፣ የማይጸብሪ ፣ የራስዳሸንና የአዲአርቃይ አካባቢዎች ትግራይ ክልል ዉስጥ የሚጠቃሉ ሲሆን በመተማ በኩል ደግሞ የተወሰነውን ክፍል ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለመስጠት ድርድር በመካሄድ ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የየከተማዎቹ ባለስልጣናት ለኢሳት በሰጡት መረጃ መስረት ባለስልጣናቱ የህዝቡን የልብ ትርታ አዳምጠዉ የህዝብን ሀዘንና ድንጋጤ የተመለከቱ ሲሆን፣ አንዳንድ የወረዳ ባላስልጣናት ደግሞ የችግሩን ስፋት ኢሳት ለህዝብ ይፋ እንዲያሳዉቅላቸዉ ተማጽነዋል። የወያኔ አገዛዝ ከአሁን በፊት በአማራ ክልል ስር የነበረውን የመተከል ዞን ለቢኒሻንጉል ጉምዝ፤ ራያና ቆቦን፤ ዳንሻንና ሁመራን በመተማ በኩል ለሱዳን፤ ቀሪውን የመተማ ክፍል ደግሞ ለቤንሻንጉል መሰጠቱን በማውሳት፣ አሁንም ተጨማሪ መሬት እየተቆረሰ ክልሎችን ለማስደሰት ሲባል ብቻ እኛን እየተጎዳን ነው በማለት ቅሬታቸውን ገልጸዋል። የአንቀጽ 39 ትሩፋቶች የሰጡን ገፀ በረከቶች ናቸው ሲሉ ያማረሩት የድንበር ከተማ ነዋሪዎች ደግሞ "ጨለምተኛ አባት መሬት እየሸጠ ልጆቹን ርስት ያሳጣል። ጨለምተኛ መንግስት ደግሞ አገርን በመሸጥ ዜጎችን ያስደፍራል፤ ማንነታቸውን ያሳጣል፤ መንግስትም ማንነታችንን እየነጠቀን ነው ሲሉ" በወያኔ አገዛዝ ላይ ያላቸዉን ከፍተኛ ቅሬታ ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ በእሳት የተቃጠሉ አብያተ ቤተክርስቲያናት ለፖለቲካ ፍጆታ አየተጠቀመ ነዉ

ምስራቅ ጎጃም ዉስጥ አዋበልና አነደድ በሚባሉ ወረዳዎች የሚገኙ ስምንት አብያተ ክርስትያናት ከሚያዚያ እስከ ነሐሴ ባለው የአምስት ወር ጊዜ ዉስጥ በእሳት ተቃጥለው መዉደማቸዉንና በቤተክርስቲያናቱ ውስጥ የሚገኙ ንዋየ ቅድሳት፣ ልዩ ልዩ አልባሳትና መጽሐፍትም የእሳቱ ሰላባ መሆናቸዉን ምስራቅ ጎጃም ዉስጥ የሚገኙ የዜና ወኪሎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። በቃጠሎዉ እጅግ ያዘኑት የአካባቢው ነዋሪዎች በመንግስት በኩል የቃጠሎዉ ምክንያት ባስቸኳይ ተመርምሮ በወንጀለኞቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም ሰሚ ጆሮ እንዳላገኙ ዘጋቢዎቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው በክልሉ ቴሌቪዥን በዜና መልክ እንዲገለፅ ያደረጉት ጥረትም አለመሳካቱ ታዉቋል፡፡

በአንድ አካባቢ ብቻ በተለያየ ጊዜ አብያተ ክርስትያናት በተደጋጋሚ ሲቃጠሉና ንብረት ሲወድም በአገር ውስጥ መገናኛ ብዙኋን አንድም ቀን አለመዘገቡ ወንጀሉ የመንግስት እጅ እንዳለበት በግልጽ ያሳያል ሲሉ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ሰዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ዘጋቢያችን ያናገራቸዉ አንድ የምስራቅ ጎጃም የባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤት ሰራተኛ አብያተ ቤተክርስቲያናቱ መቃጠላቸውን አረጋግጠዉ በቃጠሎው የተነሳ በህዝብና በመንግስት በኩል እንዲሁም በህዝቡና በቱሪዝም ኮሚሽን በኩል ከፍተኛ ውዝግብ መነሳቱን ተናግረዋል። መንግስት ድርጊቱን የፈጸሙት የሙስሊም አክራሪዎች ወይም የማህበረ ቅዱሳን አባላት ናቸው ሲል፣ ህዝቡ ደግሞ አክራሪዎች አይደሉም በማለት እየተከራከረ መሆኑን ሰራተኛው ጨምሮ ገልጿል። የባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤትም የችግሩ መነሻ በውል ባይታወቅም በአክራሪዎች ምክንያት እንዳልሆ በውል እንደሚያምን አክለው ገልጸዋል።

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## መብቱን ለማስከበር ታስሮም እንደማያጎበድድ በእስር ላይ የሚገኘው አንዷለም አራጌ አረጋገጠ

ፋሽስት ወያኔ ባቀነባበረው የውሸት ክስ በሽብርተኝነት ተከሶና በወያኔ አሻንጉሊት ዳኞች እድሜ ልክ ተፈርዶበት ቃሊቲ ወህኒ ቤት የሚገኘው የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ አንዳለም አራጌ ዛሬም በእስር ቤት ለመብቱ እየታገለ እንደሆነ ተገለጸ። በውጭ ያሉት የተቃውሞ ሃይሎች መሰባሰብና እየተጠናከሩ መምጣት ሰላም የነሳው ፋሽስት ወያኔ በሀገር ውስጥ በቁጥጥሩ ስር ባለው የፓርቲዎች ሰላማዊ ሰልፍ እንቅስቃሴ ላይ ዛቻ እንዲያሰማ እንዳደረገው ይታወሳል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነው እንግዲህ ፋሽስት ወያኔ ለአቶ አንዷለም አራጌ ሰላም በማሰብ በሚል በእስር ቤት የሚጠይቁትን ሰዎች ቁጥር ለመወሰን የፈለገው።

ፋሽስት ወያኔ ከሌሎች የቀዩ እስረኛ ጓደኞቹ ጋር እንዳይገናኝ በማሰብ እስካሁን ድረስ አቶ አንዷለም አራጌን በጊዜያዊ ማቆያ ውስጥ ማሰሩ ሳያንስ ይህን የነጻነት ታጋይ የሚጎበኙ ሰዎች ቁጥር ለመገደብ በመወሰን እነማን እንዲጎበኙት እንደሚፈልግ ስም ዝርዝር እንዲያቀርብ ጥያቄ ማቅረቡ አንዷለምን አበሳጭቷል ተብሏል። በማንኛውም ጊዜና ቦታ ለመብቱ እንደቆመ አስረግጦ በማሳየት ላይ ያለው አንዷለም ግን "መጎብኘት ሕገመንግስታዊ መብቴ ነው ። የስም ዝርዝርም አልሰጥም" በማለቱ የተነሳ ከመስከረም 29 2006 ዓ/ም ጀምሮ ማንም ሰው እንዳይጎበኘው ክልከላ መጣሉን ፓርቲው አንድነት አሳውቋል።

ፖለቲከኛና ሚስማር ሲመታ ይጠብቃል የሚሉ ወገኖች የነጻነት ታጋዩ የሞራል ፅናትና ጥንካሬ ከመቼውም በላይ መድረሱን አድንቀው፤ ፋሽስት ወያኔ የደረሰበት የወረደና የዘቀጠ የፍርሃት ደረጃ ግን በእስር ቤት አጉሮ እያሰቃያቸው ያሉትን የነፃነት ታጋዮች እስካለማመን አድርሶታል ያላሉ። እውነት አስፈሪ ናት የሚሉት እነዚሁ ወገኖች ሕገመንግስታችን የሚሉትን ተረት ተረት እንኳ ሳይቀር ከፋሽስት ወያኔ በተሻለ ሁኔታ የነጻነት ታጋዩ አንዷለም አራጌ አሳምሮ እንደሚያውቀውና እያከበረው መሆኑን የሚያውቀው ሕሊናቸው ጫፍ ከሌለው ፍርሃት ውስጥ እንደከተታቸውም ጨምረው ጠቁመዋል።

## በወያኔው ብአዴን ውጥረት የነገሰበት ግምገማ ከ 170 በላይ አባላት በአንድ ጊዜ መልቀቂያ እንዳስገቡ ተጠቆመ

ሁልጊዜም በያመቱ የአባላት ግምገማ (በሂሳብ ሰዎች አጠራር የሰዎች ኢንቬንተሪ) የሚያካሂደው ፋሽስት ወያኔ፤ የታመመ፣ የደከመ፣ ተነሳሽነት የጎደለው እንዲሁም ሌላል ሌላም በሚል ሰበብ፤ የፖለቲካ አቋም መስመራቸውን ያላስተካከሉ የሚላቸውን እንደሚቀጣ ይታወቃል። በዚህ መሰረትም ብአዴን የሚባለው የወያኔው አንዱ አንጃ ኪራይ ሰብሳቢነት በሚል አጀንዳ የጀመረው ግምገማ ከፍተኛ ውዝግብና መተረማመስ ከመፍጠሩም በላይ በስብሰባው የተገኙ አባላት በብአዴንና በወያኔው አገዛዝ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ በማሰማት ላይ መሆናቸው ታውቋል።

"ባይናችን እያየነውና እየሰማነው ካለው በአገዛዙ ሹመኞች የሚከወን ንቅዘት አንጻር እኛን እስክርቢቶ ወሰዳችሁ እያሉ መገምገም ፌዝ ነው" ያሉት የግምገማው ተሳታፊዎች "በሚሊዮን ዶላር በሚቆጠር መጠን ወደ ውጭ ሀገራት ባንኮች የሚወጣውን ሃብት መቆጣጠር የተሻለ ነበር" ሲሉ በምሬት ተናግረዋል። አክለውም "ልጆቻችንን በቅጡ ለመመገብና ለማሳደግ ካቃተን አባላት ላይ የአባልነት ክፍያ እያለችሁ ትሰበስባላችሁ ሌላው ግን አገዛዙ የቸረውን የአገዛዝ ቦታ ተጠቅሞ ከሕዝብ በዘረፈው ሃብት ሶስትና አራት ሕንጻዎችን ሲገነባ የሚናገረው የለም፤ እኛም መረረን መኖር አቃተን በዚሁ ሳቢያም አባላት መልቀቂያ እያስገቡ ነው ብለዋል።"

## የፋሽስት መለስ ሙት መንፈስ ወራሽ ሃይለማሪያም ደሳለኝ በሕዝባችን የመሰለፍ መብት ላይ ማላገጡ ተገለጸ

ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ ከዚህ በኋላ የሚደረጉ ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎችን ልንከለክል እንችላለን ማለቱ ተሰማ። በተደጋጋሚ ጠንካራ ሰልፎችና ስብሰባዎች ሲጨናነቅ የከረመው ፋሽስት ወያኔ፤ የሰላማዊ ሰልፉን አስተባባሪዎችንም ሆነ ሰልፈኞችን ለመወንጀል አሸባሪ ከሚላቸው ድርጅቶች ጋር ተጠጋግተዋል በማለት ሲለፍ ከቆየ በኋላ በስተመጨረሻ ከናካቴው መብታቸውን በመገደብ ሰልፉን ሊከለክል እንደሚችል ፍንጭ ሰጠ። ሕዝብ የመሰለፍ መብት እስካለው ድረስ መሰለፍ ይችላል የሚለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ መከልከልን ለምን እንዳመጣው ለብዙዎች ግልጽ አይደለም።

ሕዝብም የመሰለፍ መብት ወያኔም የመስማት ግዴታ አለባቸው የሚሉ ወገኖች ሕግና ስርአት እስካልጎደለ፣ ዝግጅቱ በሰላም እስከተጠናቀቀና ሕዝቡም ጥያቄየ አልተመለሰም ብሎ እስካመነ ድረስ ባንድ ጉዳይ ብቻ ያሻውን አህል ጊዜ ሰልፍ ማድረግ ይችላል ይላሉ። ይህ ካልተደረገ ደግሞ ወደሌሎች የሃይል አማራጮች መግባታቸው አይቀሬ ነው ይላሉ። ፋሽስት ወያኔ ግን ለራሱ የፖለቲካ ጫወታ እስካልጠቀመው ድረስ ለምንም ነገር ደንታ የሌለው ጉጅሌ መሆኑን ባለፉት የአገዛዝ ዘመኖቹ በተግባር ሲያሳይ እንደነበር ይታወሳል።

## አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ !!!

ኃይለማሪያም ደሳለኝ በአንድ ወቅት ዉሸትን የማያዉቅ ጠንካራ ክርስቲያን ነዉ ተብሎ ሲነገርለት ሰምተን ነበር፤ ታድያ ይህ ሰዉ መለስን ሲተካ ብዙዎች በጥርስ የለሽ አንበሳነቱ ቢስማሙም ዉሸት እንደ ንጉስ በነገሰባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ዉሸት የማያዉቅ መሪ መጣ መባሉ ብዙዎቻችንን ነጻነት የተገኘ ያክል አስደስቶን ነበር። ሆኖም ከወያኔ ጋር የዋለ ሰዉ እራሱን ሆኖ መክረም አይችልምና ኃይለማሪያምም ባስቀመጡት ቦታ የማይገኝ የሌላ መንደር ሰዉ ሆኖ ተገኘ። በዚህም የዜጎችን ተስፋ አመከነ፤ ደስታቸውንም ወደ ኃዘንና ትካዜ ለወጠው።

ባለፈዉ ሳምንት መጨረሻ ላይ በመገናኛ ብዙኋን ፊት ያየዉን አላየሁም፤ የሰማዉን አልሰማሁም፤ ያልሆነዉን ሆነ የሆነዉን ደግሞ አልሆነም እያለ ሽምጥጦ አደርጎ የካደዉ ኃይለማሪያም ደሳለኝ፤ በእርግጥም ጎበዝ የመለስ ዜናዊ ተማሪ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል። ኃይለማሪያም ባለፈዉ ዓርብ አንድ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶ ነበር። ይህ ግለሰብ በዚህ ጋዜጣዊ መግለጫዉ ኢትዮጵያን ያክል ትልቅ አገር ከሚመራ ሰዉ ቀርቶ ከአንድ ተራ የቢሮ ተላላኪ እንኳን የማይጠበቅ መልስ ሲመልስ ተስተዉሏል።

ኃይለማሪያም በጋዜጣዊ መግለጫዉ ወቅት ከቀረቡለት ብዙ ዲሪቶ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ አገር ቤት ውስጥ እየተደረገ ያለው ሠላማዊ ሰልፍ ጉዳይ ነበር። ኃይለማሪያም አገር ቤት የሚደረጉ የተቃውሞ ሰልፎች *"በራሳቸው የሚደረጉ ሳይሆኑ ከኋላ ባሉ ሌሎች ኃይሎች መሪነት የሚደረጉ"* ናቸው ሲል ተናግሯል። ኃይለማሪያም ጌቶቹ ፊቱን በጨርቅ አስረዉት የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር፤ መከራና ስደት አልታይ ብሎት ነዉ እንጂ ወያኔን የመሰለ ነብሰ ገዳይ ባለበት አገር ዉስጥ የህዝብን ብሶት የሚያስጋቡ ጥያቄዎች በየቀኑ ይመነጫሉ እንጂ ከዉጭ አገርማ አይመጡም። በሌላ በኩል ደግሞ ይሄዉ ኢትዮጵያ በቅርቡ ያፈራቸዉ ዋሾ ሰዉ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚያደርጉት ሠላማዊ እንቅስቃሴ የአሸባሪዎች እጅ ያለበትና፤አማኞቹ ሃይማኖታቸውን የወደዱ መስሏቸው ሳያውቁ የገቡበት ስለሆነ እንዲታረሙ እንመክራቸዋለንም" ብሏል። እዚህ ላይ በግልጽ እንደምናየዉ ኃይለማሪያም ደሳለኝ እመራዋለሁ የሚለዉን ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ፈጽሞ ሊረዳ አልቻለም፤ ስለዚህ ምክር የሚያስፈልገዉ መብትና ነጻነት ምን እንደሆኑ ገብቶት የሚታገለዉ የአትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን ኃይለማሪያም እራሱ ነዉ።

እኛ ግንቦት ሰባቶች ወያኔን የመሰለ ጨካኝ እና ምንም አይነት አገራዊ ኃላፊነት የማይሰማውን ዘራፊና ዘረኛ ቡድን በሠላማዊ መንገድ የሚጋፈጡ ወገኖቻችንን እናደንቃለን። እነዚህ ወገኖቻችን ኃይለማሪያም ደሳለኝ እንደሚለው የማንንም አጀንዳ የተሸከሙ ሳይሆኑ የራሳቸው የሆነ አጀንዳ ያላቸውና ኃይለማሪያም በዉክልና ለሚያስረግጣቸዉ ወገኖቻችዉ መብትና ነጻነት የሚታገሉ ጅግኖች ናቸዉ። አጀንዳቸውም የተደበቀ ወይም ከጀርባውም ሌላ ነገር ያለው አጀንዳ አይደለም።አጀንዳቸው ግልጽ እና የታወቀ የነፃነት፤ የእኩልነት፤የፍትህና የሠላም አጀንዳ ነው። ኃይለማሪያም ደሳለኝ የዜጎችን ጥያቄ አድምጦ መልስ መስጠት ሲገባው እነዚህን የኢትዮጵያን ህዝብ አጀንዳ ተሸክመው የሚታገሉ ወገኖች ደካሞች አድርጎ ለመሳል የሚያደርገዉ ሙከራ አንድም በተቃዋሚዎቹ ዙሪያ የተሰባሰበውን የሰው ኃይል ካለማወቅ፤ አለዚያም ደግሞ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ይሏታል ጅግራ" እንደሚባለው ነገር ነው።

ሌላው ኃይለማሪያም የሚናገረዉ ቃል ጠፍቶት በተደጋጋሚ ሲንተባተብ የታየዉ በሽብርተኝነት አካባቢ የተጠየቀዉን ጥያቄ ሲመለስ ነዉ። በእኛ እይታ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዋነኛው አገር በቀል አሸባሪ ህወሃት እና ህውሃት ብቻ ነው።ህወሃት ስልጣን ላይ ያቆየኛል ብሎ ከገመተ የማይመሰርተው የክስ ዓይነት፤ የማያፈሰው የንጹህ ሰው ደም፤ የማያፈነዳው የቦንብ እና የፈንጂ ዓይነት እንደሌለ ከሃውዜን እስከ አዲስ አበባ ያሉ መንገዶች ቋሚ ምስክሮች ናቸው። ይህንን እኩይ ተግባሩን ዓለም ሁሉ እንደሚያውቀው በዊክ-ሊክ ላይ የወጣው መረጃም አሳይቷል።

የህወሃት ታማኝ ሎሌ የሆነዉ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ሠላማዊ ትግሉን ለማፈን ከፈለገ በትግሉ ዙሪያ የተሰባሰቡትን ዜጎች ከሌላ ከማንም ጋር ማነካካት አያስፈልገውም። ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ ሁሉ አንደ ኃይለማሪያም ሞቶ የተቀበረን ሰዉ ራዕይ የተሸከሙ የአመለካከት ደሃዎች ሳይሆኑ የራሳቸው አስተሳሰብና ህያዉ ራዕይ ያላቸው ዜጎች ናቸው። እነዚህን ሠላማዊ ታጋዮች ከማይገናኝ ሌላ ኃይል ጋር አቆራኝቶ ለመምታት መሞከር ለኃይለማሪያምም ሆነ ለጌቶቹ አይበጃቸዉም። ዛሬ በወያኔ ነብሰ ገዳይ ወታደሮች ተከብቦ እዩኝ እዩኝ የሚለዉ ኃይለማሪያም ደሳለኝም የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጣ የነደደ ቀን ደብቁኝ ማለት ይመጣልና ያ ቀን ከመምጣቱ በፊት የበደለዉን ህዝብ ይቅርታ ጠይቆ የነጻነት ኃይሎችን እንዲቀላቀል ወገናዊ ምክራችንን እንለግሳለን።

በመጨረሻም ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ስለ ግንቦት ሰባት ተጠይቆ ሲመልስ ግንቦት ሰባት "በህልም ውስጥ ያለ ድርጅት" ነው ብሏል። ታድያ ምነዉ ተኝቶ ህልም የሚያልም ድርጅት ኃ/ማሪያምንና ጌቶቹን እንዲህ ያቃዣቸዋል? ለምንስ ይሆን ወያኔና ታማኝ ሎሌዉ ኃ/ማሪያም ያገኙትን ሁሉ ግንቦት ሰባት እያሉ የሚያስሩት፤ የሚደበድቡትና የሚገድሉት? ያገኛችሁትን ሁሉ የግንቦት ሰባት አባል እያላችሁ ትከሳላችሁ? ለምንስ በግንቦት ሰባት ስም ታስራላችሁ? ትገርፋላችሁ? ትገድላላችሁ? ተኝቶ ለሚያንቀላፋ ድርጅት ለምን ትሸበራላችሁ፤ ለምንስ እንቅልፍ አጥታችሁ ትባዝናላችሁ? ግንቦት ሰባት እናንተ አልገባችሁም እንጂ መነሻውንና መድረሻውን አጥርቶ የሚያውቅ፤ ከደመናው ባሻገር ፍንትው ያለ የነፃነት ዉጋገን የሚታየው ባለ ታላቅ ራዕይ ድርጅት ነው። እስኪ ምናልባት ቢገባችሁ ተረት ቢጤ እንንገራችሁ፤

*አንዲት ሚዳቋ ነበርች አሉ። ሚዳቆ ከመሬት ገንዘብ ተበድራ ሲትኖር ከእለታት አንድ ቀን መሬት አፍ አውጥታ ብድሬን መልሽ እንጂ ብላ ትጠይቃታለች። ሚዳቆዋም ደንግጣ ከነበረችበት ቦታ ፈትለክ ብላ ወደ ተራራ ጫፍ ላይ ወጥታ እፎይ ያንን ድምጽ ከአሁን በኋላ አልሰማም አለች። መሬትም በይ ብሬን ክፈይኝ ስትል ዳግም ጠየቀቻት። እንዴ ይህች መሬት የሌለችበት ዬት አገር ሊሂድ ብላ ሚዳቆ ወደ ማይታወቅ ቦታ ተፈተለከች። ከዚያም እያለከለከች በቃ አሁንስ አታገኚኝም ስትል አሁንም መሬት ብቅ ብላ እየጠበኩሽ ነውኮ ብድሬን ክፈይ እንጂ ስትል ጠንከር አድርጋ ጠየቀቻት።ሚዳቆዋም መሬት የሌለችበት ልትደረስ ስትበር ስትበር ሳንባዋ ፈንድቶ ሞተች"ይባላል።*

የፍትህ፤ የእኩልነት፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች እንደ መሬት ናቸው። የትም ሂዱ፤ የትም ግቡ ይከተሏችኋል።መስጊድ ዉስጥ አሉ፤ ቤተክርስትያናት ውስጥ አሉ። ቤተመንግሰት ዉስጥም አሉ። የሌሉበት ቦታ የለም። መፍትሄው እንደ ሚዳቆዋ መሸሽ አይደለም። መፍትሄው ዜጎች የሚያነሷቸውን የፍትህ፤ የእኩልነ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን አድምጦ ትክክለኛ መልስ መስጠትና ከዕዳ ነጻ መሆን ብቻ ነዉ። ከዚህ ዉጭ ጥያቄን ላለመስማት ወይም ሰምቶ ለመደፍጠጥ የሚደረገው ከንቱ ሩጫ መጨረሻው እንደ ሚዳቆዋ መፈንዳት እንጂ ህይወት አይሆንላችሁም።

እኛ ግንቦት ሰባቶች ዘረኛዉንና አሸባሪውንና የወያኔ ስርዐት ለመደምሰስና ህዝብ በነፃነት ያለፍርሃት የሚኖርበትን አገር ለመፍጠር ቆርጠን ተነስተናል። ከእንግዲህ የሚያቆመን ምንም ነገር የለም። የምንታገለዉ ለህዝብ ጥያቄያችንም ህዝባዊ ጥያቄ ነዉና እኛም እንደጥያቄዉ በየመስጊዱ፤ በየቤተክርሲቲያኑና በየሰፈሩ ዉስጥ አለን። እኛ የሌለንበት ስፍራ የለም። በዚህ አጋጣሚ የዘመናት ትግላችን ፍሬዉ የሚታይበት ቀን እጅግ በጣም ቅርብ ነዉና የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም አገር ተረካቢ የሆነዉ ወጣቱ ትዉልድ እራሱን፤ ወገኖቹንና እናት አገሩን ለማዳን የሚደረገዉን የነጻነት ትግል እየመጣ እንዲቀላቀል ወገናዊ ጥሪያችንን አቅርበናል። ኑ እና ተቀላቀሉን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ወያኔ አንዳንድ የአማራ ክልል ከተሞችን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከዚህ በተጨማሪ ሁኔታው ያበሳጫቸው ነዋሪዎች በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ድርጅቶች ጉዳዩን አጽንኦት ሰጥተው ሊያዩት ይገባል ብለዋል። ይህ በእንዲህ አንዳለ የትግርኛን ቋንቋ የአማራ ክልል ተማሪዎች እንዲማሩት ለማድረግ ታስቦ በጎንደር በተካሄደው ፓይለት ጥናት ህዝባዊ ተቃውሞ በማስነሳቱ እንዲቆም ተደርጓል። ይህንን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ ጥናት ባለሙያ የሆኑት ፕሮፌሰር ባየ ይማም በቅርቡ በአቀረቡት ጥናት የመንግስት ቋንቋ አጠቃቀም 'የህዝብን ጉዳይ በህዝብ ቋንቋ' የሚለውን መርህ የተከተለ ባለመሆኑ ህዝቡ ማግኘት ያለበትን መልእክት በትክክል እያገኘ፤ ለለውጥም እየተነሳሳ አይደለም ብለዋል፡፡ ባጭር ቃል በዚህ አይነት ቋንቋ የሕዝብን አእምሮ መቀየር እንደማይቻል የገለጹት ፕሮፌሰሩ፣ባለስልጣናቱ የአማረኛ ቋንቋ እንዲጠፋ የበኩላቸውን እየተወጡ ነው ብለዋል፡፡"ሀገራችን የቋንቋ ፖሊሲና የአጠቃቀም ደንብ ወይም ስርዓት እስካሁን የላትም፡፤ እስካሁን ድረስ ከህገመንግስታዊ የመብት ማረጋገጫ አንቀጾች ያለፈ፣ ቋንቋን እንደ ማንኛውም የሀገር ሀብት በእቅድ የሚያሳድግ፣ የሚቆጣጠር፣ አጠቃቀሙን ስርዓት የሚያሲይዝ ፖሊሲና ዝርዝር ደንብ የለንም፡፡ ባለመኖሩም ሁሉም እንደፈለገ የሚተረጉምበት፣ የሚጽፍበት፣ የሚያሰራጭበት ሁኔታ ውስጥ ገብተናል፡፡ ይህ ሊቆምና ቋንቋዎቻችን በዕቅድ ሊያድጉና ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል" ሲሉ ፕሮፌሰሩ ተናግረዋል። የአማርኛ ቋንቋ የሀገሪቱ የስራ ቋንቋ መሆኑ እየታወቀ ክልሎች በፍፁም ጥላቻ እንዲመለከቱትና እንዲሁም ክፍል ውስጥ ገብተው የመማርን መብት ለተወላጆች ብቻ ትቻለሁ በማለት የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ፤ በትግራይ ፤ በኦሮምያና ደቡብ ክልሎች ክፍት እንደሚሆኑ ታዉቋል። ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት በሚመዱበበት ወቅትም በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጡ ደጋፊ ትምህርቶችን ላለመማር አሰጣ አገባ እንደሚገቡ ታውቋል፡፡በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በቤንሻንጉል እና ሶማሌ ክልሎች የክልሎቹን ቋንቋ የማይናገሩ ተማሪዎች ተመርቀው ስራ ለማግኘት አይችሉም። በመሆኑም ከአማራ ክልል የሚመጡ ተማሪዎች ከክልላቸው፣ ከአዲስ አበባ እና ከደቡብ ክልል ውጭ በሌሎች ክልሎች ተቀጥረው ለመስራት እየተቸገሩ ነው።አንዳንድ ልዩ ችሎታ ያላቸው ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ለመስራት ካልሆነ በስተቀር የአማራ ክልል ተማሪዎች ስራ ለመያዝ እንደሚቸገሩ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ሰዎች ገልጸዋል። በሌላ በኩል ግን አማርኛ የሚችል የማንኛውም ክልል ተወላጅ በአማራ ክልል ተወዳድሮ ስራ የመያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

---

## ዘመነ ፍዳው እንዲያጥር ለምትፈልጉ ወገኖች ሁሉ! (ክፍል 2)

(ይነጋል በላቸው)

2. በትጥቅ ትግል ላይ ነን የሚሉ እንደግንቦት ሰባት ያሉ ድርጅቶች በዚህ ዙሪያ ትልቅ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፤ ይቻላቸዋልም:: ጋዜጠኛ ግሩም ቅድም እንደጠቆመውና ሁላችንም እንደምንገነዘበው ሀገር ማለት ተራራና ወንዝ ብቻ ማለት አይደለም፤ ሀገር ማለት ዛፍና ቅጠል ማለት ብቻም አይደለም፤ ሀገር ማለት በዋናነት ሕዝብ ማለት ነው:: ለሕዝብ ቆሜያለሁ የሚል አርበኛ ደግሞ በቅድሚያ በምንም መንገድ ሊከፋፈል እንደማይገባው መረዳት አለበት - ተከፋፍሎ ለመጓዝ ከቆረጠ ከሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ይልቅ የራሱን - ምናልባትም ከሥልጣን ጋር የተያያዘ - ጥቅምና ፍላጎት አስቀድሟል ማለት ነውና ከሕዝብ ልብ እየወጣ ይሄዳል - ያም ዱሮውን ገብቶ ከሆነ ነው:: ሕዝብ በማንኛውም ረገድ እንጦርጦስ ወርዶ፣ ሀገር የእፉኝቶች መፈንጪያ ሆና፣ ዘረኝነት ድሩን አድርቶ ጥቂቶች አለሀፍረትና አለአንዳች ይሉኝታ በብዙዎች ላይ የሚምነሸነሹበት አስከፊ ሥርዓት ተፈጥሮ፣ የኑሮ ውድነቱ አብዛኛውን ሸማች ከገበያ አውጥቶትና ለከፋ ድህነት ዳርጎት፣ በተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ሥውርና ግልጽ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ታውጆ፣ የሙያ ማኅበራትና የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ድራሻቸው እንዲጠፋና በምትካቸው የወያኔ ሥሪት የሆኑ ኮንዶማዊ ድርጅቶች አገር ምድሩን በሸፍጥና በተንኮል ሥራ አጥለቅልቀው በማይረቡ ጥቅማ ጥቅሞች በትምህርት ያልገፉ ድሃ ዜጎችን እያማለሉ፣ ቄስ መስቀሉን ኢማሙ ክታቡን ኅሊናን ለሚያሳውር የዘረኝነት ዓላማና ለሆዳቸው ሲሉ ሸጠው ለውጠው፣ አማኑኤል ሆስፒታል በፖለቲካውና በኑሮ ብስጭት በሚያብዱ ዜጎች ከአፍ እስከገደፉ ጢም ብሎ እየሞላና በድንኳን እየተስተናገዱ፣ የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾችና ሰላማዊ ተቃዋሚዎች ዘብጥያ እየወረዱ ወይም እየተገረፉና እየተገደሉ ሀገር ማቅ ለብሳ፣ ከሞላ ጎደል ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች በሞራልም በሃይማኖትም ሙልጭ ወጥተው ሆዳምነትና ስግብግብነት እየተንሰራፋ እንዲሄድ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ ሀገር ወደባድማነት እየተለወጠች በምትገኝበት አደገኛ ሁኔታ በጎጥና በዘር ተደራጅቶ ይህን ሥር የሰደደ ጠላት ራሱ በመጣበት መንገድ አሸንፈዋለሁ ብሎ መነሣት የሚያዋጣ አይደለም ብቻ ሣይሆን ይህን ድጥ የበዛበት መንገድ መሞከሩ ራሱ የሕዝብን ችግር ከማባባስ ባሻገር የፈየደው ነገር እንደሌለ ከልምድ መረዳት ዐዋቂነት ነው - አሁን ዘግይቶም ቢሆን:: አልበርት አነስታይን እንዳለው አንድን ችግር ለመፍታት ችግሩ በተፈጠረበት የአስተሳሰብ ጎዳና መጓዝ የሚያዛልቅ አይደለም፤ የተሻለ አስተሳሰብንና የላቀ አስተዋይነትን ይዞ መገኘት ይጠይቃል:: መጽሐፉም ይላል፡- ‹ብዔል ዘቡል ብዔል ዘቡልን አያስወጣም›:: ስለዚህም በትጥቅ ትግል የተሰለፉም ይሁኑ ሌሎች ተቃዋሚዎች በአንድነት ሆነው በመታገል የዚህን ሕዝብ ሰቆቃ ማስወገድ ይገባቸዋል - አለበለዚያ እነሱም ከወያኔ ባልተናነሰ በችግራችን መራዘምና እየገዘፈ መሄድ በኃላፊነት የሚጠየቁበት ጊዜ ይመጣል፤ ይህን አጠቃላይ እውነት ሁሉም ወገን ሊገነዘበው ይገባል - እየመሰለን እንጂ ከታሪክ ፍርድ ማምለጫ የማሳበሪያ መንገድ በጭራሽ የለም:: ለአሁኑ አጣዳፊ ችግር ደግሞ በአንዳንድ ሀገራት - ለምሳሌ በየመን - የጋራ ግንባራቸውን ተወካዮች በመመደብ ለወገናቸው ያላቸውን ፍቅርና ቅን አሳቢነት ማሳየት አለባቸው፤ የተበተኑ ወገኖቻችንም አለኝታ እንዳላቸውና እንደወያኔው ያለ የሚሸጣቸው የቀን ጅብ ሣይሆን ተቆርቋሪ ወገን እንዳላቸው ማሳወቅ ወቅቱ የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው:: ይህን ነገር ለነገ የሚያሳድሩት ጉዳይ ሳይሆን የዲፕሎማሲው ሥራ ዛሬውኑ መጀመርና ልዩ ትኩረት አግኝቶ ተግባራዊ መሆን ይገባዋል - እርግጥ ነው - ድርጊት የንግግርን ያህል ቀላል እንዳልሆነ ግልጽ ነው፤ ግን ይሞከር - እንዲሁ በየስብሰባውና በየቃለ መጠይቁ ‹ሕዝብ፣ ሕዝብ› ወይም ‹ኢትዮጲያ፣ ኢትዮጵያ› ማለት ብቻውን ጉንጭን ማልፋት ነው፤ የወገን ፍቅር ይኑረን - ያንንም በተግባርና ለማስመሰል ሣይሆን ከእውነት እናሳይ፤ አናቱን የሚያሳክከውን እግሩን ብናክለት ኅሊናችንም ታካኪውም ይታዘቡናልና በአፋጣኝ እንለወጥ፤ በሞተ ሕዝብ ላይ ለመንገሥ ከምንራወጥ የሚሞተውን ሕዝብ ጠላቶቻችን ናቸው ብለን ከፈረጅናቸው ወገኖች ጋርም ቢሆን “ተመሳጥረን” እናድነው፤ ከወገን ጋር ተባብሮና ተመሳጥሮ ሕዝብን ከመግደል ይልቅ ከጠላት ጋር ተባብሮ ሕዝብን ማዳን በፈጣሪም በታሪክም ታላቅ ዋጋ አለውና አሁን ለአቃቂርና ለወሬ ስለቃ ጊዜ እንዲኖረን ፈቃዳችን አይሁን:: ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ደግሞ ሁሉም ወገን መተባበር አለበት:: ወገን እየተሰቃዬ፣ እየተሰደደ፣ አካሉ እየተቆራረጠና ለመለዋወጫነት እየተሸጠ ... ባለበት የሚዘገንን ሁኔታ በድሎትና በቅንጦት መኖር፣ ገንዘብንም በአልባሌ ሥፍራና ለአልባሌ ተግባር ማዋል በእግዚአብሔር ዘንድ በኃጢኣተኝነት ባይሆንም እንኳን በነውረኝነት ሳያስፈርጅ የሚቀር አይመስለኝም:: እናም ከዚህ አንጻር ብዙዎቻችን ብዙ መሥራት፣ ራሳችንንም በጥሞናና በተመስጦ መፈተሽ ይጠበቅብናል:: በተለይም እዬዬም ሲደላ ነውና ሕዝባችን ላይ የተሰኩትን እሾሆች ለመንቀል ምንም ጥረት ሳናደርግና ፈቃደኝነት ሳይኖረን እርስ በርስ በነገር ጦር ብንጠዛጠዝ ታሪክ ምሮ አይምረንም::

በመሠረቱ ሕዝብ ሲባል ያ ደንቆሮ የወያኔው የየመን ኤምባሲ ሠራተኛ እንደተናገረው በገረድና በአሽከር ወይም በባለሥልጣንና በከበርቴ የሚመደብ ሳይሆን ውሻና ድመትም እንኳን ቢሆኑ በኢትዮጵያ አፈር፣ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተፈጠረ ሁሉ በየፈርጁ ክብርና ሞገስ ያለው ፍጡር መሆኑን መረዳት ይገባል:: ክርስቶስ አለ፡- እኔ የመጣሁት ለጻድቃን አይደለም - ለኃጥኣን እንጂ:: አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ዜጎችን ባለውና በሌለው፣ በተማረና ባልተማረ፣ በቀላና በጠቆረ፣ ባጠረና በረዘመ፣ ... እንዲሁም በዚህና በዚያ ሃይማኖትና ፆታ ተመሥርቶ እያዳላ የሚፈርድ ወይ የሚያስተዳድር ከሆነ ያ ሰው ‹ሰው ነኝ› ባይል ይሻለዋል:: ይህ ዓይነቱ አሠራር በፈጣሪም ህግ በዓለምም ህግ የተወገዘ ኃጢኣትና ወንጀልም ነው:: ዜጋህን እንዴት ‹ለገረድ አልመጣንም› ትላለህ? ምን ዓይነት ልበድፍንነት ነው? እንዲህ ዓይነት ደደብ ዜጎች በኃላፊነት ብቻ ሣይሆን በተራ ዜጋነት በሚገኙባት ሀገር መፈጠር ራሱ አያስጨንቅም ትላላችሁ? ጋዜጠኛ ግሩም ይህን ጽሑፍ ካነበብክ እባክህን የዚህን ሰውዬ ስምና መለያዎች መዝግበህ ያዝ፤ የሕዝብ ጊዜ ሲመጣ ለፍርድ አቅርበን ለምንና ለነማን ወደየመን እንደተላከ እናስጠይቃለን:: ይህን የምለው የበቀለኝነት ስሜት ተጠናውቶኝ እንዳይመስላችሁ - በፍጹም - ግን ሁላችንም በምንሠራው ሥራ መለካትና መዳኘትም ስለሚኖርብን ነው - ከሞትን በኋላም ቢሆን:: ለምሳሌ በጉጉት ከምንጠብቀው ነጻነት በኋላ አቶ መለስን ለመክሰስ ከተዘጋጁ ሰዎች መካከል እኔ አንዱ ነኝ:: - ጣሊያን ሀገር እንዲህ ሆነ አሉ፡- አንድ ሕጻን እየተጫወተ ሳለ ለውሃ በተቆፈረ 36 ሜትር ጠባብ ጉድጓድ ውስጥ ይገባል:: የአካባቢው ሰዎችና ባለሥልጣናት ያን እምቦቀቅላ እንዴት እንደሚያወጡት እየተጨነቁ ሳለ የሀገሪቱ መሪ (ፕሬዝደንት ወይ ጠ/ሚ) ከተፍ ይላል:: ለካንስ ወሬውን በዚያው ቅፅበት በተባራሪ ሰምቶ ኖሯል:: ይህ የሀገር መሪ እንደሕዝቡ እየተጨነቀ፣ እያለቀሰና እያጽናና ሸሚዙን ሰብስቦ በላብ እየተጠመቀ አብሮ ሰው የሚሠራውን ሥራ መሥራቱን ይቀጥላል - ከልቡ::... የዜግነት ግዴታ፣ የመሪነት ግዴታ፣ የሰብኣዊነት ግዴታ፣ የአለኝታነት መንፈስ ... ማለት እንዲህ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን ኖሮስ? ‹እኔ ለአንድ ሕፃን አልተሾምኩም!› ሊባል ነው? ወይንስ እንደፔፕሲ ማስታወቂያ ‹ተጨማሪ ይጠይቁ› ይሉን ይሆን? የምንገርም ሕዝብ ከሚገርሙ መሪዎች ጋር! አይደል? መበታተን ይነሰን ታዲያ? ለወገኑ የማያስብና ከፋፋይ ዘረኛ እንዴት ባለሥልጣን ሊሆን ይችላል?

እግዚአብሔር ሆይ ሰው ሹምልን - ሰው አማረን፤ ሰው ናፈቀን:: እንደሰው የሚያስቡና ጠረናቸው ሰው ሰው የሚል ሰዎች እንዲመሩን ወደሥልጣን አምጣልን:: ጅቦችና ዓሣማዎችን ከላያችን አንስተህ፣ ዘረኞችንና ማይም ሆዳሞችን ከጫንቃችን አውርደህ፣ ሀገራዊና ወገናዊ ስሜት የሌላቸውን በጮማና ዊስኪ የደነዘዙና የደነበሹ ባለሥልጣኖችን በቃችሁ ብለህ ለወገንና ለሀገር የሚቆረቆሩ፣ ሕዝባችን ተራበ ተራቆተ ብለው ሌት ከቀን የሚጨነቁ እውነተኛ የሀገር መሪዎችን ስጠን::ከሚገባን በላይ ተቀጥተናልና አሁንስ ምሕረትህን ላክልን፤ እንደቸርነትህ እንጂ እንደሥራችን ግን አይሁንብን:: የጥንቱን መተሳሰብና ፈሪሃ እግዚአብሔርንም መልስልን:: አሜን::

3. በየኤምባሲዎች የምትገኙ የወያኔ ባለሥልጣናት ደግሞ እንዲህ አድርጉ፤ በግልጽ ለወገን መቆርቆራችሁ ከተደረሰበት ከሥራ ልትታገዱ ወይም የከፋ የቂም በቀል እርምጃም ሊወሰድባችሁም ይችላል - በመበቀል ወያኔን የሚስተካከል የለምና:: ስለዚህ ሥቃይ ላይ የሚገኙ ወገኖቻችሁን በድብቅና በእጅ አዙር ለመርዳት ሞክሩ:: በዚህ የተቀደሰ ተግባራችሁ ቢያንስ ትውልዳችሁን - የራሳችሁን ልጆችና የልጅ ልጆች - ከቅጣት ትታደጋላችሁ:: እንደምታውቁት እነመለስ ልጅ አልወጣላቸውም:: ይህም የሆነው የእርጉማን ልጆች በመሆናቸው እንጂ የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ጥራት ስለጎደላቸው እንዳይመስላችሁ - ራሳቸው እነመለስም ቢሆኑ አብዛኞቹ የባንዳና የጠላት አሽከር ልጆች በመሆናቸውና በዚያም ምክንያት የሀገራዊና ሕዝባዊ እርግማን ተረካቢዎች በመሆናቸው ያገኙትን ዕድል ለነሱና ለሀገራቸው በሚጠቅም መልኩ አልተጠቀሙበትም - ዕድለቢስነታቸው ያሳዝናል፤ ወደውና ፈቅደው እንዳልሆነ ግን ዕንወቅላቸው:: እግዚአብሔር አንድን ሕዝብ ሊቀጣ ሲፈልግ ጨካኝ ንጉሥ እንደሚሾም ቀድሞውን በመጽሐፍም የተጠቆመ ነውና በነዚህ የእፉኝት ልጆች ሰበብ የእኛም የብዙኃኑ የቀደመ ኃጢኣት ታጠበ፤ የቀረን የንስሓው ጊዜ ነውና ከየተዘፈቅንበት ... አረንቋ እየወጣን ኅሊናችንን በማጽዳት ወደነጻነት አምባ ለመውጣት እንሞክር - እግዚአብሔር እንደማይረሳን በፍጹም ልባችን እንመን - አንድ እርምጃ ወደርሱ እንቅረብና እርሱ ወደኛ ዐሠርና ሃያ እርምጃዎችን እንደማይመጣ እንታዘበው - ‹በኔ ይሁንባችሁ› አልላችሁም - እኔም ምንም አይደለሁምና - ለትህትና አይደለም - ባይሆን በወደድኩ - ምክንያቱም በሀገራችን አንድ ሎጥ እንኳን ቢገኝ ኖሮ ምን ያህል የእግዚአብሔር ፀጋ እንደሚበዛልን እረዳለሁና - ሁላችን እንደጠፋን የማምን ነገር ግን ወደርሱ ብንመለስ ትንሣኤያችን በቅጽበት ውስጥ እውን ሊሆን እንደሚችል የምገነዘብ ኃጢኣተኛ ኢትዮጵያዊ ነኝ:: አለበለዚያ ... ምዕመናን ... ነገር አለ! ... ፈጣሪ ከተጨማሪ የደም ባሕር ይሠውረን:: በነገራችን ላይ እርግማን ትውልድን እንደሚመትር ወይ እንደሚያመክን ብዙ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ማስረዳት ይቻላል:: የበረከትን፣ የስብሃትን፣ የሰዓረን፣ የተፈራን፣ የ‹ሐጎስ›ን፣ የ‹አብረኸት›ን ልጆች ብታዩዋቸው ትገረማላችሁ፤ ታዝኑማላችሁ:: ለካንስ እርግማን ያለዘር የማስቀረት ኃይል አለው? ብላችሁ ትደመማላችሁ:: የወያኔ ባሪያዎች ግን ባለቻችሁ አጭር ጊዜ ጥሩ ሥራ በመሥራት ከዚህ ሕዝባዊና ሀገራዊ እርግማን ነጻ ልትወጡ ትችላላችሁ:: መልካም ዕድል በደጃችሁ አለች:: .....

( ክፍል 3 ሣምንት ይቀጥላል)

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አክራሪነትና ሽብረተኝነት ላይ ስልጠና እንዲወስዱ እያስገደደ ነዉ

እሱ እራሱ ሽብርተኛ የሆነዉ የወያኔ አገዛዝ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ባሉ የትምህርት ተቋማት ስለ አክራሪነት፤ ሽብርተኝነትና ጸረ ሰላም እያለ ስለሚጠራቸዉ ኃይሎች መስጠት የጀመረዉን ስልጠና ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ለመስጠት ማቀዱ ተሰማ። የኢትዮጵያ ትልቁ ችግር ዘረኝነት፤ ሙሰኝነትና የሰብዓዊ መብቶች መደፍጠጥ መሆኑን በዉል ለሚረዳና የእነዚህ ሁሉ ችግሮች ምንጭ ደግሞ ወያኔ መሆኑን ለተገነዘበ ህዝብ ወያኔ አክራሪነትና ሽብርተኝነት በሚል ስልጠና መስጠት መጀመሩ ህዝቡ ልቡ እንዲሸፍት ከማድረግ ዉጭ ምንም ዉጤት የማይኖረዉ ከንቱ ድካም መሆኑን አንዳንድ የወያኔ አባላትን ጨምሮ ብዙዎች ይስማሙበታል። በተለይ እንዲህ አይነት ስልጠና ለህጻናት ጭምር መሰጠቱ ብዙዎችን አስቆጥቷል። ለምሳሌ ከሁለት ሳምንት በፊት በክልል ለሚገኙ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞችና መምህራን ስልጠናው በተሰጠበት ወቅት፣ በርካታ ተሳታፊዎች እድሜያቸው ከ15 አመታት በታች የሆኑ ተማሪዎች ስልጠናውን እንዳይወስዱ ጠይቀው ነበር።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴክኖሎጂ ፋኩልቲ ተማሪዎች ባለፈው አርብ እና ቅዳሜ ለአዲሱ የትምህርት ዘመን ለመመዝገብ ወደ ግቢ በገቡበት ሰአት፣ ምዝገባ ቆሞ ተማሪዎች ስድስት ኪሎ ወደሚገኘው የስብሰባ ማእከል እንዲያቀኑ ከታዘዙ በኋላ በአዉቶቡሶች እየተጫኑ ወደ ስልጠና ቦታ ተወስደዉ ያለፍላጎታቸዉ ቀኑን ሙሉ ስልጠናዉን ሲከታተሉ ዉለዋል። በስልጠናዉ ወቅት የወያኔ ካድሬዎች ለአገዛዙ አደጋ ይፈጥራሉ ብለዉ ያመኑባቸዉን እንደ ግንቦት7፣ ኦነግና ኦብነግ የመሳሰሉትን ድርጅቶች በጸረ ሰላምነትና በአሸባሪነት እንደምሳሌ ተጠቅመዉባቸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኦሮሚያ ክልል ከአክራሪነት ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው ስልጠና የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ለ10 ቀናት ተዘግተዋል። በከፍተኛ የአመራር ደረጃ የሚገኙ የኦህዴድ ባለስልጣናት ለ10 ቀናት በአዳማ ከተማ በአክራሪነት እና ሽብርተኝነት ዙሪያ ስልጠና ሲሰጣቸው ከቆየ በሁዋላ፣ አሁን ደግሞ ስልጠናው ወደ ታች አመራር አባላት በመውረዱ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች የሚገኙ ሰራተኞች ለ10 ቀናት ያክል ጽህፈት ቤቶቻቸውን ዘግተው ስልጠናውን እየወሰዱ ነው።

አገልግሎት ፈላጊዉ ህዝብ ጉዳዩን ለማስፈጽም ወደ ተለያዩ መስሪያ ቤቶች ሲሄድ ባለስልጣናቱ ስልጠና ላይ ናቸው የሚል መልስ እየተሰጠ ነው። መንግስት በዚህ ስልጠና ምን ለማግኘት እንዳሰበ በግልጽ ባይታወቀም ስልጠናው ወደ ወረዳዎች ሁሉ ይዘልቃል ተብሎአል። እስካሁን ድረስ በስብብሰባው ላይ የሚቀርቡት አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኛው ተሰብሳቢ በኢትዮጵያ ውስጥ አክራሪነት አለ ብሎ አያስብም። ይህ ደግሞ ወያኔን ክፉኛ እንዳስደነገጠዉ ለማወቅ ተችሏል።

## ወያኔ ሦስኛዉን ትርጉም የለሽ ፕሬዝዳንት ሾመ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ላለፉት 12 አመታት በአምባሳደር ሽኝትና ቅበላ ባገለገሉት በመቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ምትክ በቱርክ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩትን ዶክተር ሙላቱ ተሾመን በዘመነ ወያኔ የአገሪቱ ሦስተኛ ፕሬዚዳንት አድርጎ መሾሙን ከሰሞኑ ከወደ አዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ። የኦህዴድ አባል የሆኑትና የዛሬ 12 ዓመት ፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳን ይተካሉ ተብሎ ይወራላቸዉ የነበሩት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ በወቅቱ የፓርቲ አባል የሆነ ሰዉ ፕሬዚዳንት መሆን አይችልም በሚል ሰበብ መዘለላቸዉ የሚታዉስ ነዉ። ፈረንሳይኛ፤ እንግሊዝኛና የቻይና ቋንቋ አጣርተዉ እንደሚናገሩ የሚነገርላቸዉ ዶክተር ሙላቱ ተሾመ ትርጉም የለሹን የይስሙላ ሹመት ሲረከቡ በህዝብ ተወካዮችና በፌዴሬሽን ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር፥ ምክር ቤቶቹ የጣሉባቸውን አደራና ሐላፊነት ባላቸው አቅም ሁሉ ለመወጣት ቃል ከመግባታቸውም ባሻገር ከአገርና ከህዝብ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በሃላፊት እንደሚወጡ ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ፕሬዚዳንት የመሆን ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው በሬዲዮ ፋናና በማህበራዊ የመገናኛ አዉታሮች ሲናገር የሰነበተዉ አትሌት ሀይሌ ገብረስላሴና ብዙ የተባለላቸዉ የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ባልደረባ የሆኑት ወይዘሮ ሙሉ ሠለሞን ለዉድድር እንኳን ለመብቃት እንዳልቻሉ ለማወቅ ተችሏል። በመቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስን የሚተካዉ ሰዉ በህዝብ ተወካዮችና በፌዴሬሽን ምክር ቤት ይመረጣል ሲባል እዉነትም ምርጫ ያለ መስሎት ፕሬዚዳንት ለመሆን ቋምጦ የነበረዉ አትሌት ሀይሌ ገብረስላሴ አሁን ቁርጡን ስላወቀ ወደሚያዉቅበትና ታላቅ ሰዉ ወዳደረገዉ ወደ ሩጫዉ መመለሱ ታዉቋል።

## ዘጠኝ አመት ሙሉ ኤኮኖሚዉ በድርብ አኃዝ አደገ እያለ የዋሸን ወያኔ ዘንድሮ ዉሸቱን መደበቅ አቃተዉ

ላለፉት ዘጠኝ አመታት አንዴ የአገሪቱ ኤኮኖሚ በድርብ አኃዝ አደገ ሲለን ሌላ ግዜ ደግሞ ህዝብን መቀለብ ያቃተዉን የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የአለማችን አምስተኛዉ ፈጣን አኮኖሚ ነዉ እያለ ሲያታልል የከረመዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፈዉ በጀት ዓመት የአገሪቱ ኢኮኖሚ 9 ነጥብ 7 በመቶ ማደጉን አስታወቀ። ይህ 9 ነጥብ 7 በመቶ የተባለዉ ቁጥር የዋጋ ንረት መስተካከል ይደረግበት አይደረግበት ወይም ቁጥሩ እራሱ ትክክለኛ ቁጥር ለመሆኑ በሦስተኛ ወገን ባይረጋገጥም የወያኔ ባለስልጣኖች ግን ከአሁኑ እድገቱን ማድነቅ ጀምረዋል፡፡ ለምሳሌ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታው አብርሃም ተከስተ በበርካታ ፈተናዎች ዉስጥ በምናልፍበት ወቅት እንዲህ አይነት እድገት ማስመዝገብ መቻላችን የሚወደስ ነዉ ብሏል።

በዚህ በወያኔዉ የገንዝብ ሚኒስቴር መ/ቤት በተሰራጨዉ ሪፖርት ላይ በ2005 በጀት አመት የአገሪቱ ግብርና ዘርፍ 7 ነጥብ 1 በመቶ፤ የአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ የ4 ነጥብ 9 በመቶ እድገት እንዳስመዘገቡ የተጠቀሰ ሲሆን የሃገሪቱ ድህነት በ2003 ከነበረበት 29 ነጥብ 6 በመቶ ወደ 26 በመቶ ዝቅ ማለቱም በሪፖርቱ ላይ ተጠቅሷል። የወያኔ አገዛዝ ከሁለት አመት በኋላ በሚጠናቀቀው የአምስት አመት የእድገት እቅድ መንግስት የ14 በመቶ እድገት እንደሚያስመዘግብ የገለጸ ቢሆንም። ባለፉት ሦስት አመታት በታዩት የእድገት አህዞች መሰረት አገዛዙ የእቅዱን ግማሽ ያክል እንኳ ማሳካቱን ብዙዎች የሚጠራጠሩ ሲሆን አለማቀፉ የገንዘብ ድርጅት አይ ኤም ኤፍ የኢትዮጵያን የ2005 አመት የእድገት ትንበያ ወደ 5 ነጥብ 6 በመቶ ዝቅ ማድረጉ ይታወሳል።

## የደቡብ ክልል ፖሊሶች የሪፖርተር ጋዜጣን ማኔጂንግ ኤዲተር አስረዉ ወደ ክልላቸዉ ወሰዱ

ባለፈዉ ሐሙስ መስከረም 30 ቀን 2006 ዓ.ም. እኩለ ቀን ላይ የደቡብ ክልል ፖሊሶች አዲስ አበባ ድረስ መጥተዉ መላኩ ደምሴ የተባለዉን የሪፖርተር ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር አስረዉ ወደ ክልሉ ዋና ከተማ ወደ አዋሳ መዉሰዳቸዉን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ። ፖለሶቹ ጋዜጠኛዉን የያዙት ቦሌ መድኃኔዓለም አካባቢ በሚገኘው የሪፖርተር ጋዜጣ ቢሮ ዉስጥ በመግባት ሲሆን ጋዜጠኛዉ ወደ አዋሳ ከመወሰዱ በፊት ወደ ቦሌ ክፍለ ከተማ በፖሊስ ጣቢያ የተወሰደ ሲሆን፣ በኋላም ለክልሉ ፖሊስ አባላት ተላልፎ መሰጠቱን ሪፖርተር ጋዜጣው ዘግቧል፡፡

ጋዜጠኛ መላኩ ደምሴ ታስሮ ለጥያቄ አዲስ ወደ አዋሳ የተወሰደዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ረቡዕ ነሐሴ 29 ቀን 2005 ዓ.ም. በጋዜጣው የፊት ገጽ ላይ «የደቡብ ክልል ሦስት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች ከኃላፊነት ተነሱ» የሚል ያልተረጋገጠ ዜና በመዘገቡ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን ሪፖርተር ጋዜጣ ዜናዉ መሰረተ ቢስ መሆኑን ተረድቶ በቀጣይ ዕትሙ እሑድ ጳጉሜን 3 ቀን 2005 ዓ.ም. ላይ ዜናው በወጣበት የጋዜጣው የፊት ገጽ ላይ ማስተካከያ ማውጣቱ ይታወሳል፤ ሆኖም የደቡብ ክልል ባለስልጣኖች እንዴት ተደፈርን በሚል ይመስላል የክልሉን ፖሊሶች አዲስ አበባ ድረስ በመላክ ስህተቱን አምኖ እርማት ያወጣዉን ጋዜጠኛ አስረዉ ወደ ክልላቸዉ ወስደዉታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ አዋሳ የሚገኘዉ የሪፖርተር ጋዜጣ ባልደረባም ይህንን ዘገባ በማጠናቀርና በመዘገብ ለሠራው ስህተት ዝግጅት ክፍሉ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዱን አክሎ ገልጿል፡፡

በተመሳሳይ ዜና እዚሁ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የሊያ መጽሔት አዘጋጆች አንድ “ረጂም እጅ” አለኝ ባይ በባለሀብት ግለሰብና መንግስት ከፍተኛ በደል አንደፈጸሙባቸዉ ገለጹ። ከወያኔ ባለስልጣኖች ጋር በፈጠረዉ ግንኙነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ባለሀብት መሆን የቻለ ግለሰብ ለማስታወቂያ ስራ ለመክፈል ቃል የገባዉን 36 ሺህ ብር ከለከለን የሚሉት የሊያ መጽሔት አዘጋጆች የራሳቸዉን ገንዘብ በተከለከሉ “የባለሀብቱን ስም አጥፍታችሁዋል” ተብለው ወደ ማዕከላዊ ፖሊስ ጣብያ ተወስደዉ ቃል እንዲሰጡ መደረጋቸዉን ገለጹ። አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና መሰረት ከወያኔ አገዛዝ ጋር ባለዉ ንኪኪ በአጭር ጊዜ ዉስጥ የአሉሙኒየም ፋብሪካ ባለቤት መሆን የቻለዉ ይሄዉ ግለሰብ ከሊያ ጋዜጣ ጋር በመስማማት ለረዥም ጊዜያት ድርጅቱን ሲያስተዋዉቅ መቆየቱን ለማወቅ ተችሏል። ሆኖም በቅርቡ የማስታወቂያውን ክፍያ እንዲፈጽም በጋዜጣው ሲጠየቅ ከእኔ ፍላጎት ውጪ የሆነ ነገር ጋዜጣችሁ ላይ አዉጥታችኋል በማለት ክፍያውን ለመፈጸም ፈቃደኛ እንዳልሆነና ጭራሽ ክፈል ተብሎ ሲጠየቅ ”እርፋችሁ ተቀመጡ፤ አምስት ሳንቲም አልሰጣችሁም። አርፋችሁ የማትቀመጡ ከሆነ እጄ ረዥም መሆኑን አሳያችኋለሁ” በማለት ዝቶባቸዋል።

በተፈጸመባቸው ክህደትና በደል ያዘኑት የሊያ መጽሔት አዘጋጆች በመጽሔቱ ቅጽ 2 ቁጥር 35 ህትመት ላይ” እጄ ረዥም ነኝ ባዩ ባለሀብት ገመና ሲፈተሽ”በሚል ርዕስና በመስከረም 18/2006 ዕትም ስለባለሀብቱ የምርመራ ዘገባ ከመስራታቸውም በላይ የደረሰባቸውን ነገር በዝርዝር የገለጹ ሲሆን፤ በዚህም ጽሑፍ ሳቢያ በባለሀብቱ የስም ማጥፋት ክስ ተመስርቶባቸው ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ቀርበው የመኪና ሊብሬ እና የንግድ ፈቃድ በማስያዝ በዋስ ተለቅቀዋል። ኢትዮጵአ ዉስጥ ጋዜጠኞችን በሆነዉ ባልሆነዉ ማሰር የተለመደ ሲሆን ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብትና የፕሬስ ነጻነት የማይታወቅባት ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን በማሰር በአለም ላይ ተወዳዳሪ የላትም።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org